
የመስቀሉ ስብከት
ትምህርት 2 ለ ሐምሌ 4፣ 2018


“የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ
ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።”
(1 ቆሮንቶስ 1:18)

በ1 ቆሮንቶስ 1:17-31 ላይ መስቀሉ የሰዎችን ህይወት እንዴት እንደሚለውጥ ተጽፎልናል።

ለአማኞች መስቀሉ የመዳን ምልክት ነው። ነገር ግን በ1ኛው ክፍለ ዘመን ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች መስቀሉ የአንድን ወንጀለኛ አሳፋሪ ሞት የሚወክል ነበር።


በመስቀል ላይ ሞቶ ከዚያም የተነሳ ሰው ሊያድን ይችላልን? ይህ ሀሳብ ለሰዎች የሞኝነት፣ ትርጉም የሌለውና ደካማ የሆነ ሀሳብ ነው። ነገር ግን ለመንፈስ ቅዱስ ጥሪ ልባችንን ለከፈትነው መስቀሉ “የእግዚአብሔር ኃይል [...] ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም” ነው (1ቆሮ 1:18፣ 30)።







- የእግዚአብሔር ጥበብ
- የመስቀሉ እብደት
- የእግዚአብሔር ኃይል
- የመስቀሉ ስብከት
- የእግዚአብሔር ሞኝነትና ድካም




# የእግዚአብሔር ጥበብ

“ለተጠሩት ግን፥ አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።” (1 ቆሮ 1:24)

ጳውሎስ በአቴና ጠቢባን ሰዎችን ያሳምን ዘንድ የሰውን ጥበብ ለመጠቀም ሞክሮ ነበር። ከዚያን ጊዜ አንስቶ መለኮታዊ ጥበብን ብቻ ለመጠቀም ወሰነ።

እግዚአብሔር መልዕክቱን እንዲሰብክ የላከው “የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም” (1ቆሮ 1:17)።



በጳውሎስ የተሰበከው መለኮታዊ ጥበብ ምንድን ነበር?

የእግዚአብሔር ጥበብ “የጠቢባንን ጥበብ” የሚያፈርስ፣ “የአስተዋዮችንም ማስተዋል” የሚጥል ነው (1 ቆሮ 1:19)፤ “እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን?” (1ቆሮ 1:20)።

የእግዚአብሔር ጥበብ ከሰው አሳብ በተቃራኒ “በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።” (1 ቆሮ 1:21)።



# የመስቀሉ እብደት

"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፥" (1 ቆሮንቶስ 1:23)



ሞሪያ/mōria የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉሙ እብደት፣ ጅልነት፣ ሞኝነት ሲሆን በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ 5 ጊዜ በጥቅም ላይ ውሏል:

- "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።" (1 ቆሮ 1:18)
- "በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።" (1ቆሮ 1:21)
- "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም[...] ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፥" (1 ቆሮ 1:23)
- "ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም" (1ቆሮ 2:14)
- "የዚህች ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና" (1 ቆሮ 3:19)



መስቀሉ ለጠፉት ሞኝነት ነው፤ እነዚህ እግዚአብሔርን የማያውቁት አሕዛብ፣ ስለዓለም ብቻ የሚያስቡ፣ በራሳቸው ጥበብ ብቻ የሚመሩ ናቸው።


ነገር ግን መስቀሉ ለዳኑት በረከት ነው፤ እነዚህም መስቀሉን እግዚአብሔር ባየበት መንገድ የተመለከቱት ናቸው።

# የእግዚአብሔር ኃይል

"የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።" (1 ቆሮንቶስ 1፡18)

መስቀሉ የሰውን እጅግ የከፋ ማንነት የእግዚአብሔርን ደግሞ ታላቅነት ያሳያል (1 ቆሮ 1:18)።

| የሰው ክፋት | የእግዚአብሔር ታላቅነት |
| --- | --- |
| ስርዓት አልበኝነት | ኃይል |
| ጥላቻ | ሁሉን መቀበል |
| ለራስ አደጋ መሆን | ይቅር ባይነት |
| በራስ ላይ ፍርድን ማከማቸት | መዳን |



መስቀሉን የማይቀበሉ ሰዎች የክፉ ስራቸውን ውጤት ያጭዳሉ በመጨረሻም ባልተቀበሉት በእርሱ የሚጠፉ ይሆናል።

በመስቀሉ ላይ የታየው የእግዚአብሔር ኃይል ሰውን ኃጥያቱን በሙሉ ይቅር በማስባል ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀው ሙሉ አቅም አለው፤ የዘላለም ሕይወትንም ያስገኝለታል (ቆላ 1:20፣ 1ጴጥ 2:24)።

# የመስቀሉ ስብከት



“በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፥ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።”
(1 ቆሮንቶስ 1፡21)

**የመስቀሉ ስብከት እንደ ሞኝነት የሚቆጠረው ለምንድን ነው (1 ቆሮ 1:21-24)?**



አይሁድ ከሮም ጭቆና የሚያወጣቸውን መሢህ ሲጠባበቁ ነበር። ኢየሱስ በመስቀል እንደሚሞት በሚናገርበት ወቅት የራሱ ደቀ መዛሙርት እንኳ ይደነግጡ ነበር። በተጨማሪም በአይሁድ አስተሳሰብ በእንጨት ላይ ተንጠንጥሎ የሚሞት ሰው በእግዚአብሔር የተረገመ ነው (ዘዳ 21:23)። ከነአካቴው አዳኝን ሲጠብቁ ላልነበሩት ለአሕዛብ ደግሞ ምላሹ ተመሳሳይ ነው፤ መስቀሉ ሞኝነት ነው።

ነገር ግን ለመላዕክት የመስቀሉ ስብከት ፍጹም የተለየ ነበር። በሰማይ ያመልኩት የነበረው ኢየሱስ ያልተቀበሉትን የሰው ልጆች ወድዶ ሊሞትላቸው ፈቀደ። ጳውሎስ በስብከቱ ሊያስተላልፍ የፈለገው ሀሳብ ይህ ነው።

የመስቀሉ መልዕክት እግዚአብሔር ለእኛ መዳንን ለመስጠት የሄደበትን ርቀት ያሳያል።

# የእግዚአብሔር ሞኝነትና ድካም



"ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና።" (1 ቆሮንቶስ 1:25)

እግዚአብሔር በማንኛውም መንገድ ቢሆን ሞኝ ወይም ደካማ ይባላልን (1 ቆሮ 1:25)?

እርግጥ ነው አይባልም ምክንያቱም እግዚአብሔር ምንም ጉድለት የለውም። ጳውሎስ እዚህ ጋር ተምሳሌታዊ ንጽጽሮሽ እያደረገ ነው። እግዚአብሔር የሞኝነት ሀሳብ ቢኖረው ከሰው እጅግ ጠቢብ ከሆነው ሀሳብ ይልቅ ጥበበኛ ይሆናል፤ ወይም እግዚአብሔር ደካማ ሙግት ቢኖረው እጅግ ብርቱ ከሚባሉት የሰው ሙግቶች ይልቅ ይበረታል።



እጅግ ጠቢብ ከሚባሉት ሰዎች የተሰበሰበው ጥበብ እንኳን ለሰው ልጆች የመዳንን እቅድ ሊያዘጋጅ አይችልም።

በመስቀል ላይ በቀረበው የኢየሱስ መስዋዕትነት ኃይል በኩል "ለሚድኑት" (1 ቆሮ 1:18)፣ "ለሚያምኑት" (1 ቆሮ 1:21)፣ እና "ለተጠሩት" (1 ቆሮ 1:24) እግዚአብሔር ብቻ ቤዛነትን ሊሰጥ ይችላል።

ለመንፈስ ቅዱስ ጥሪ _ምላሽ_ በመስጠት በኢየሱስ _የሚያምኑት_ ብቻ _እንደሚድኑ_ እናስተውል።



“በዚህ ዘመን በሚኖሩ በብዙሃን አእምሮ ውስጥ የቀራኒዮ መስቀል በተቀደሱ ትውስታዎች የተከበበ ነው። ከስቅለት ትዕይንት ጋር ቅዱስ ሀሳቦች ይያያዛሉ። ነገር ግን በጳውሎስ ጊዜ መስቀሉ የሚታየው በአስቀያሚና አሰቃቂ ስሜት ነበር። ሞትን በመስቀል ላይ የተገናኘውን ሰው የሰው ልጆችን ሁሉ አዳኝ አድርጎ ከፍ ማድረግ ፌዝንና ተቃርኖን ማስከተሉ የማይቀር ነው። [...]

መስቀሉን ከሰው ዘር መከበር ወይም ከሰው ልጅ መዳን ጋር በምንም አይነት መንገድ ለማገናኘት መሞከሩ ሰዎች ደካማ አስተሳሰብ እንዳለው እንዲያስቡ ያደርገው ነበር።

ነገር ግን መስቀሉ ለጳውሎስ በጣም ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ነው። [...] ከግል ልምምዱ እንደተረዳው አንድ ኃጥያተኛ የአብን ፍቅር በልጁ መስዋዕትነት ውስጥ ሲመለከትና ለመለኮት ምሪት እጅ ሲሰጥ የልብ መለወጥ ይከተላል ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ክርስቶስ ሁሉ ነገሩና በሁሉ ውስጥ ይሆናል።”

EGW (The Acts of the Apostles, p. 245)